# 2023 የማህበረሰብ ጤና ፍላጎት ጋር የተያያዘ የግምገማ ውጤቶች

healthy montgomery
DHHS MONTGOMERY COUNTY Department of Health and Human Services
MONTGOMERY COUNTY MARYLAND 1776

## አስፈላጊ የጤና ፍላጎቶች

### የባህሪ (Behavioral) ጤና እና የአደንዛዥ እጽ ጉዳቶች ጋር በተያያዘ አገልግሎቶችን ማግኘት

የአእምሮ ጤናን መጠበቅ የተሟላ ጤናን ለማግኘት በጣም አስፈላጊ ነው። የአዕምሮ፣ የባህሪ እና የአደንዛዥ እጽ መጠቀም ጋር በተያያዘ አገልግሎቶችን ማግኘት ለአንድ ሰው ስሜታዊ፣ ስነ-ልቦናዊ እና ማህበራዊ ደህንነት ከፍተኛ አዎንታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል ብሎም ጤናማ ማህበረሰብ ለመፍጠር ቁልፍ ሚና ይኖረዋል።

### እንደ ትምህርት ፣ ገቢ ፣ የመኖሪያ ቤት ፣ የሥራ ቅጥር ፣ ምግብ እና የግል ማህበራዊ አገልግሎቶች ያሉ የሰብአዊ አገልግሎቶችን ማግኘት

እነዚህ አገልግሎቶች የተሟላ ጤናን ለማግኘት ወሳኝ ናቸው። መሰረታዊ ፍላጎቶችን ለሟሟላት እንዲቻል ተገቢው የሰብአዊ አገልግሎቶች ካልቀረቡ የማህበረሰቡ አባላት የላቀ ጤናማ ህይወት ሊያገኙ አይችሉም።

### የቴክኖሎጂ አገልግሎት ማግኘት

ዲጅታል ዲቫይድ “Digital divide” እንደ ኢንተርኔት አገልግሎት፣ ኮምፒውተሮች እና ሞባይል ስልኮች ያሉ አስተማማኝ ቴክኖሎጂዎች ባላቸው እና በሌላቸው ማህበረሰቦች መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል። ቴክኖሎጂን የመጠቀም እድል (digital divide) በጤና እንክብካቤ ማግኘት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። የቴክኖሎጂ አገልግሎት አለማግኘት ጤና እና የጤና ልዩነቶች እንዲጨምሩ ከሚወስኑ አንዱ ማህበራዊ ተግዳሮት ነው።

### ተገቢ እና ደረጃውን የጠበቀ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት ማግኘት

የመጀመሪያ ደረጃ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የተለመዱ በሽታዎችን እና ጉዳቶችን ለመከላከል እና ለማከም የመጀመሪያ የበሽታ መከላከያ መንገዶች ናቸው። የጤና እንክብካቤ ለማግኘት ውስንነት ያለባቸው ግለሰቦች ያሉባቸው ማህበረሰቦች ዝቅተኛ የአኗኗር ሁኔታ የሚኖራቸው ሲሆን ረዥም እድሜ የመኖራቸው እድል ዝቅተኛ ነው።

### የፓርኮች፣ የህዝብ መገልገያዎች ፣ የጤንነት መጠበቂያዎች እና የመዝናኛ አገልግሎቶችን ማግኘት

ፍትሃዊ ያልሆነ የፓርኮች እና የመዝናኛ ስፍራዎች አገልግሎትን የማግኘት ሁኔታ በማህበረሰቦች ውስጥ ካሉ ሥር የሰደዱ በሽታዎች ስርጭት ጋር የተቆራኙ ናቸው።

### ጥራት ያለው የጥርስ ጤና አገልግሎት ማግኘት

መደበኛ የጥርስ እንክብካቤ ማድረግ ለጥሩ የጤና አጠባበቅ ወሳኝ ነው። በአፍ ጤንነት አጠባበቅ ላይ ያሉ የአገልግሎት ልዩነቶች ፍትሃዊ ያልሆኑ የአገልግሎት አቅርቦቶች እንዳሉ ያሳያሉ ይህም የአንድን ሰው በሙሉ ጤንነት የማደግ እድል ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል።

### የመጓጓዣ አገልግሎት ማግኘት

የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን ለማግኘት በማህበረሰቦች ውስጥ ያለው የመጓጓዣ አገልግሎት ወሳኝ ነው። ግለሰቦች የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን ለማግኘት ሲሞክሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ የመጓጓዣ ችግር ያጋጥማቸዋል ይህም በማኅበረሰቡ ነዋሪዎች ዘንድ ያለውን ስጋት እየጨመረ እንዲመጣ አድርጓል።

### የልዩ (Specialty) እና የተራዘመ የጤና እንክብካቤ ማግኘት

የልዩ (Specialty) እንክብካቤ ከመጀመሪያ ደረጃ የጤና እንክብካቤ ቀጥሎ የሚሰጥ ሲሆን የተወሰኑ የጤና አጠባበቅ ችግሮችን ለማከም  የሚሰጥ የሕክምና እንክብካቤ አገልግሎት ነው። የተራዘመ እንክብካቤ (extended care) እንደ አስቸኳይ ህክምና መስጫ ክሊኒኮች እና በቤት ውስጥ የሚሰጥ የጤና ክብካቤ ከመሳሰሉት የመጀመሪያ እና ልዩ እንክብካቤ በላይ የሆኑ አገልግሎቶችን ያካትታል። የማህበረሰብ ነዋሪዎች የስፔሻሊስት የህክምና ባለሙያዎችን ማግኘት ካልቻሉ ብዙውን ጊዜ ሥር የሰደዱ በሽታዎቻቸውን በራሳቸው እንዲወጡ ይገደዳሉ።

## ንቁ የኑሮ ዘይቤ እና ጤናማ እና የተመጣጠነ አመጋገብ

መደበኛ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እና ጤናማ የሆነ የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ለአጠቃላይ የጤና ደህንነትን እና በሽታን ለመከላከል በጣም አስፈላጊ ነው። የአካል ብቃት እንቅስቃሴ አለማድረግ እና ጤናማ ያልሆነ አመጋገብ ከዝቅተኛ የጤና ሁኔታ ጋር የተቆራኙ ናቸው ፣ ይህም ሥር በሰደደ በሽታ የመያዝ እድልን ይጨምራል።

## የባህል እና የቋንቋ ችሎታ/ግንዛቤ

የባህል እና የቋንቋ ብቃቶች ማለት ፣ የግለሰቦችን ማህበራዊ ፣ ባህላዊ እና የቋንቋ ፍላጎቶች የሚያሟሉ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶችን በጤና አጠባበቅ አገልግሎት ሰጪዎች እና በሰብአዊ አገልግሎት ባለሙያዎች በኩል ማቅረብ ነው።

## የአካባቢ ጤና

የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ጤናችንን እና ደህንነታችንን በሚያውኩ አካባቢያዊ ሁኔታዎች ላይ ያተኩራል። አካባቢያዊ ችግሮች ማለትም የአየር ብክለት፣ የውሃ ብክለት፣ የቤት ውስጥ ሬዶን (radon)፣ የሕዝብ ብዛት/ መጨናነቅ  እና ሌሎች በአካባቢው ያሉ ሁኔታዎች በሰው ልጅ ላይ የሚደርስ ጉዳትን በሽታን ወይም የሞት አደጋን ይጨምራሉ።

## ደህንነቱ የተጠበቀ እና ከረብሻ-ነጻ የሆነ አካባቢ

ግለሰቦች በማህበረሰባቸው እና በቤታቸው ውስጥ ሊደርሱ ከሚችሉ ጉዳቶች የመጠበቅ ደህንነት ሲሰማቸው ፣ የተሻሻለ አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ ስነ-ልቦናዊ እና ማህበራዊ ደህንነትን ያገኛሉ። የማህበረሰብ ደህንነት አስፈላጊነት ያልታሰበ እና ሆን ተብሎ የሚደርሱ ጉዳቶችን ይቀንሳል።

## ጉዳት እና በሽታ መከላከል እና አስተዳደር

መከላከል በጤና ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን ወይም ስጋቶችን ለመቀነስ ያለመ ነው። ጉዳት እና በሽታ የጤና እንክብካቤ ተግዳሮቶች እና እንቅፋቶች ናቸው።

## የእግረኛ ደህንነት

የእግረኛ ደህንነት ሰዎች የሚጓዙበት እና የሚጫወቱበት አስተማማኝ ቦታ እንዲኖራቸው ይጠይቃል። የእግረኛ ደህንነት የሁሉም የማህበረሰብ አባላት የጋራ ሃላፊነት ነው።

## የቆሻሻ አያያዝ

ከቤተሰብ፣ ከግብርና እና ከንግድ ተቋማት የሚሰበሰበውን የማያቋርጥ ቆሻሻን መሰብሰብ፣ ቆሻሻን መቀነስ ፣ ምርትን ደጋግሞ መጠቀም እና እንደገና መጠቀም እና ጥቅም ላይ ማዋል ፣ ቆሻሻን ጉዳት እንዳያደርስ ማድረግ (treatment) እና ማስወገድ ለህብረተሰቡ እና ለአካባቢ ጤና ጠቃሚ ነው።

## ማህበራዊ ትስስር እና የማህበረሰብ ግንኙነት

ማህበራዊ ትስስር እና የማህበረሰብ ግንኙነት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ግለሰቦች “በማህበረሰቡ ውስጥ በሚኖራቸው ግንኙነት የአብሮነት እና እንክብካቤ የማግኘት ፣ የመከበር እና ድጋፍ የማግኘት ስሜትን እንዲያዳብሩ ያግዛል ።”

## የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች ስርዓትን ማወቅ

የጤና እንክብካቤ ውጤቶችን ለማሻሻል የጤና እንክብካቤን እና የሰብአዊ አገልግሎቶችን ስርዓቶችን እና የድጋፍ አገልግሎቶችን ለማግኘት እና ለመገንዘብ እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ውስብስብ የሆነውን የዩኤስ የጤና አጠባበቅ ሥርዓትን ለመዳሰስ / ለማወቅ የሚደረግ ጥረት  መረጃ ለማግኘት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ያስከትላል ይህም ከጤና አገልግሎት የአቅርቦት ልዩነቶች ጋር የተቆራኘ ሲሆን እነዚህም በማህበረሰቦች ውስጥ ያሉ ማህበራዊ ተጋላጭነቶችን ሊጨምሩ ይችላሉ።

## የወሊድ እና ቀዳሚ የልጅነት የጤና አገልግሎት

የእናቶች እና ቀዳሚ የልጅነት ጤና በመውለድ እድሜ ላይ ያሉ ሴቶችን ጤና ከቅድመ እርግዝና እስከ እርግዝና ፣ ምጥ ፣ ወሊድ ፣ ድህረ ወሊድ እና ልጁ ከመወለዱ በፊት እስከ ጉርምስና ያለውን የጤና ሁኔታ ያካትታል። በእርግዝና ፣ በወሊድ እና በድህረ ወሊድ ወቅት ጤናን እና ደህንነትን መከታተል ለእናት እና ለልጅ ፣ ለጥሩ የወሊድ ሂደት ብሎም ለእናቶች ጤና እንዲሁም የልጅ እና የእናቶችን ሞት ለመቀነስ ትልቅ ጠቀሜታ አለው።